# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***ክፍል ሰባት** (ከክፍል ስድስት የቀጠለ)*

ከዚኽ በላይ እንዳየነው ኢዴኃቅ አዲሱ የኢሕአዴግ መሪዎች በአገራችን ላይ የተከተሉትንና ሥራዬ ብለው የተያያዙትን የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ቅኝቶች አደገኝነት ጠንቅቆ የተረዳ በመሆኑ እነኛ አደገኛ ውጥኖች በተግባር እንዳይተረጎሙ ከጥንስሱ ጀምሮ በተቻለው መንገድ ሁሉ አምርሮ ታግሏል። ሆኖም በተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶች እነኝኽን አደጋዎች ማስቀረት ቀርቶ ማዘግየት አልተቻለውም። ምንም እንኳ በአብዛኛው በአባል ድርጅቶቹ አማካይነት በስውር (በኅቡዕ) በአገር ውስጥ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ያልተቋረጠ ጥረቶች ቢያደርግም የኢዴኃቅ ጎላ ያለ አንፃራዊ ጉልበትና እርብርቡም ከአገር ውጭ ስለነበር እነዚያን እስካሁን የቀጠሉና ሥር እየሰደዱ የመጡ አገርና ሕዝብ ጎጂ የኢሕአዴግ መርኃ-እቅዶች ለማስቆም የሚጠይቀውን መሬት የያዘ ጠንካራ ትግል ማድረግ ሁኔታዎች አልፈቀዱለትም።

አጠቃላይ ሁኔታው ለአንድነትና ለሕዝባዊ ኃይሎች አሉታዊነቱ ያመዝነ ቢሆንም፤ ኢዴኃቅ በአንድ በኩል ነባርና መሠረታዊ የሚባሉ ችግሮቻችን ዘለቄታዊነት ባለው አግባባዊ መንገድ እንዲፈቱ፣ በሌላ በኩል አገዛዙ የተከተላቸው ፀረ-ሕዝብና አሉታዊነታቸው ያየለ አፍራሽ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መርኆዎችና ትልሞች በተግባር እንዳይተረጎሙ ታግሏል። ኢዴኃቅ በሚከተሉትና በሌሎች ዋና ዋና አገራዊ የመታገያ ነጥቦች (አጀንዳዎች) ላይ ለመረባረብና የተቻለውንም ለማከናወን ጥረት አድርጓል።

- ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም፤
- የለንደኑ ጉባዔ አግላይነት የሌለውና በተለይም ኅብረ-ብሔራዊ ኃይሎችን እንዲጨምር፤
- የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነት ላይ እብሪታዊ ብይኑን ያስተላለፈውና የኤርትራን መገንጠል ዋና አጀንዳው ያደረገው፣ አገራችንን ኢ-ፍትኃዊና ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ወደብ-አልባ እንድትሆን፣ ሕዝባችንን ምንም ዓይነት በታሪክም ይሁን በሕግ ላይ ባልተመሠረተ፣ ሕዝብ ሳይመክርበት በጦሰኛ የጎሣ ፖለቲካ የከፋፈለው፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነትና የሕዝቧን ሉዓላዊነት ለመሻር የተደገሰውና ሕወሓት በተናጠል ባዘጋጀውና ሽዓብያ የተሞሸረበት የአዲስ አበባው የሰኔ ጉባዔ በተዘጋጀው መልክ እንዳይደረግና ያን ማድረጉ በአገራችንና በሕዝቧ ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የቀረው ዓለም እንዲያውቀት፤
- ይኽ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች እኩይ ዓላማቸውን በተግባር ለመተርጎም እንዲመቻቸው እራሣቸው በፈጠሯቸውና ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠሯቸው አዳዲስ የጎሣ ድርጅቶች በታጀበውና ሽዓብያ "ተመልካች" በሆነበት፣ የአንድነት ኃይሎችን ባገለለ ሁኔታ እራሱን በ"ሽግግር" መንግሥትነት የሰየመ አካል የተከተለውን ሂደት ኢ-ዴሞክራሲያዊነትና ቀይቶም እራሱን ወደ-ቋሚ መንግሥትነት ሲያሽጋግር የተደረገውን አጠቃላይ የፌዝ ሂደት አደገኝነት አበክሮ በመግለፅ፤
- እራሱ ምሣሌ በመሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕወሓት-አመጣሽ የጎሣ ፖለቲካ ሰለባ ሆኖ እንዳይከፋፈልና አንድነቱን እንዳይተው፤
- እንደ-አገር መከላከያ የመሣሰሉት ብሔራዊ ተቋማት እንዳይፈርሱ፤
- የአዲስ አበባ ከፍተኛ የትምሕርት ተቋም (ዩኒቨርሲቲ) መምሕራን ላይ የተወሰደው በጠባቡ ያዬ ኀሠኛ ምንጠራ እንዲቆም፤

- ተማሪዎች አዲሶቹ ገዥዎች ኤርትራን ለማስገንጠል የተከተሉትን የተሳሳተ መሥመር በመቃወም አገር-ወዳድ ስሜታቸውንና ያላቸውን የዜግነት መቆርቆር በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ለመግለፅ በመሞከራቸው የተወሰደባቸውን ጭፍጨፋ አጥብቆ በመኮነንና በማውገዝ፤
- በአርባ-ጉጉና በሌሎች ሥፍራዎች በተለይ አማርኛ ተናጋሪ ዜጎች ላይ የአገዛዙ አጋሮችና ተባባሪዎች ያደረሱት የዘር ምንጠራ እርምጃና ጭፍጨፋ በአስቸኳይ እንዲቆና ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ፤
- በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ላይ የሕወሓት መሪዎች ኤርትራን ለማስገንጠል የወሰዱት ዓይን ያወጣ የባንድነትና የክኅደት ተግባር እንዲቆም፤
- አገዛዙ እራሱ ለቅሞ ባሰባሰባቸውና "ሕግ አርቃቂ ኮሚሽን" ብሎ በሰየማቸው ግለሰቦች አማካይነት የራሱን የፖለቲካ መርኃ-ግብር በ"ሕገ-መንግሥት" ስም በሕዝብ ላይ ለመጫን የተከተለውን ሂደትና እራሱን "ሕገ-መንሥቱን" በዝርዝር በመመርመር ስሕተቱንና አጥፊነቱን በስፋት በማስረዳት፤
- በምርጫ ስም አንድን በጠባብ መሠረት ላይ የቆመ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በመንግሥትነት ለመሰየም የተደረጉትን ጥረቶች በማውገዝና አማራጮቹን በማሳየት፤
- ለአገራችን መሠረታዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትኄ ለማስገኘት እንዲቻል ከእልህ፣ ከቂምና በቀል በፀዳ መልክ ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የሰላምና እርቅ ጉባዔ እንዲጠራና አዲስ የሽግግር ሂደት እንዲጀመር፤ ለዚኸም ተግባራዊነት የአመራር አባላቱን (ይኼው እስካሁን ድረስ በሕገ-ወጥ መንገድ በእስር የሚገኙትን አቶ አበራ የማነ-አብን ጭምር) ወደ-አገር ውስጥ ቤት በመላክ፤ ወዘተ...
- በልዩ ልዩ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና በሥነ-ጽሑፎች እንዲሁም በሣምንት ሁለት ጊዜ ለአንድ-አንድ ሰዓት በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ በሚተላለፍ የራዲዮ ሥርጭት ቀጥ ያሉ መተክላዊ መልእክቶችን ለሕዝባችን በማድረስ፤ ለአዲሶቹ ገዥዎችና ተባባሪዎቻቸው የልብ ውጋት በመሆንና ለሕዝባችንም የአንድነት አለኝታ በመሆን ታግሏል፡፡

ሆኖም ግን ያንን በሸዓብያና ሕወሓት (ኢሕአዴግ) አፍላ ጉልበት እንዲሁም በነሁላይ ትኩስ የጎሣ ፖለቲከኞች ተባባሪነትና ጉዳዩ ባልገባቸው ወይም ሊገባቸው ባልፈለጉ ወይም ሆን ብለው ሁለንተናዊ ድጋፋቸውን በለገሱ የውጭ ኃይሎች አይዟችሁ ባይነት የተያዘ የጥፋት ግሥጋሴ ኢዴኃቅ ብቻውን መፍትኄ ሊሰጠው እንደማይችል የታወቀ ነበር፡፡ በመሆኑም ኢሕአዴግ ከተባባሪዎቹ ጋር በአገሪቱ ላይ እየዘረጋ የመጣውን ከፋፋይና ፀረ-ዴሞክራሲ የአገዛዝ ሥርዓት በበቂ ለመቋቋም በውጭም ሆነ በውስጥ ያሉ አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ኃይሎችን አሰባስቦ ምክክር እንዲደረግና የተባበረ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል በማሰብ ኢዴኃቅ እንደ አንድ አካልና አባል ድርጅቶቹም በተናጠል ባደረጉት ከፍተኛ ግንባር-ቀደም ጥረትና ከሌሎች ጋር በተደረገ ትብብር በቀጣይ የምናያቸው የጋራ የትግል መድረኮች እንዲፈጠሩ አስችሏል፡፡

## ሐ- ፩፤- ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ ጉባዔ አስተባባሪ ኮሚቴ (ፓሪስ አንድ)፤-

ሕወሓት በኢሕአዴግ ስም አገራዊ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ የተከተለውን አጉል አቅጣጫ እንዲያስተካክል የአያሌ ድርጅቶች ስብስብ የሆነው ኢዴኃቅም ሆነ ሌሎች ድርጅቶች ያቀቡት የነበረውን የተናጠል ጥሪ ሰብሰብ ባለ መልክ አንድ ላይ ሆኖ መግፋቱ አማራጭ ያልነበረው ጉዳይ ስለነበር፣ የመጀመሪያው የጋራ ምክክር በፈረንሣይ አገር በፓሪስ ከተማ ተደረገ፡፡
ይኸ 'ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ፣ አገር-አቀፍ ጉባዔ አስተባባሪ ኮሚቴ' የተቋቋመው በኢሕአዴግ በሽግግር መንግሥትነት ስም አገራዊ ሥልጣን ከያዘ በኋላ አገር-ውስጥና ከአገር-ውጭ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ተሣታፊ በሆኑበት፣ ከመጋቢት ፩ እስከ ፬ ቀን

፲፱፻፹፭ ዓ/ም (March 11-13, 1993) ፓሪስ ላይ በተደረገውና 'ፓሪስ አንድ' በመባል በሚታወቀው የመጀመሪያው አገር-አቀፍ የተቃዋሚዎች ጉባዔ ነው። ይኸ ጉባዔ በሽግግሩ ሂደት ተሣታፊ የሆኑ ድርጅቶች ሣይቀር የተሣተፉበት በጊዜው መሠረተ-ሠፊ ስብሰባ በመሆኑ የተቃዋሚው ጎራ መጠነኛ ቅድሚያን የወሰደበትና ያም በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አገዛዙን ምላሽ ሰጭ (ተከላካይ) እንዲሆን ያደረገ ስብስብ ነበር።

ከሌሎች ድርጅቶች በተጨማሪ የሽግግሩ መንግሥት ምክትል የትምሕርት ሚኒስትር የነበሩት ዶ/ር በዬነ ጴጥሮስ የሐዲያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሊቀ-መንበር የደቡብ ኅብረትን በመወከል እና የሽግግሩ መንግሥት አናሣ ሽሪክ የነበረው ኦነግ ከአንበሣ ድርሻ ያዥው ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር በገጠመው ችግር ከሽግግር-መንግሥቱ እራሱን አግልሎ ስለነበር የተቃዋሚው ክፍል ባደረገው በዚኸ ስብሰባ ላይ ተሣታፊ ሆነዋል። በዚኸ 'ፓሪስ አንድ' በመባል በሚታወቀው "የሰላምና እርቅ ጉባዔ" ላይ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ)፣ የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)፣ የኢትዮጵያ ኅብረ-ብሔር ኮንግሬስ ፓርቲ (ኢኅኮፓ)፣ ትግራይ-ትግርኚ ኢትዮጵያ፣ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴኅ) እና የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አአዴአግ) ተሣታፊ ነበሩ።

ይኸ የሦስት ቀኖች ጉባዔ በወቅቱ ያለውን የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በጥሞናና በዝርዝር ገምግሞ ኢሕአዴግ የተያያዘው ሂደት ለማንም የማይበጅና ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ወደ-አልተፈለገ አፍራሽ አቅጣጫ የሚወስድ መሆኑ ግንዛቤ የተወሰደበትና በሁሉን-አቀፍ አገራዊ የሰላምና እርቅ ጉባዔ መፍትኄ እንዲፈለግለት ስምምነት የተደረሰበት ነበር። ጉባዔው የጋራ ትግሉን የሚያጠናክርና አገዛዙንም ትርጉም ወደ-አለው ድርድር እንዲመጣ የሚያስችል አስገዳጅነት ያለው ውጤትን ይዞ እንዲወጣ ለማድረግ በማሰብ ተሣታፊ ድርጅቶች በልዩ ልዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ፅሑፎች አስቀድመው እንዲያቀርቡ ተደርጓል። ጉባዔውም በነዚኸ አስቀድመው በተዘጋጁትና በዳበሩት ሰነዶች ላይ ተወያይቶ ማሰሪያ የሚሆን የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደረስና እነዚያን የስምምነት ነጥቦች የተመረኮዘ የጋራ ትግል ስልት እንዲነደፍ ጥረት ተደርጓል። ጉባዔውም አስፈላጊው ሕዝባዊ ድጋፍ እንዲያገኝና የውጭ ኃይሎችም በትክክል እንዲረዱት ሠፊ ገለፃና ግልፅነት ያለው ሂደትን ተከትሏል ማለት ይቻላል። የፓሪሱ ጉባዔ ብዙ ድርጅቶችን ባሣተፈ መልኩ በጥሩ ዝግጅት በመካሄዱና የአገሪቱን የፖለቲካ ችግር ለመፍታት የጋራ አካል ማቋቋምና ተቃዋሚው በአንድ ድምፅ ለመናገር በመቻሉ የውጭ ኃይሎችን ድጋፍና ከበሬታ እንዲሁም ተደማጭነትንም ለማትረፍ በቅቷል።

ይኸ ታሪካዊ ስብሰባ ሁሉም ኃይሎች የሚሣተፉበት አገር-አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባዔ ከጥቅምት ፭ እስከ ፱ ቀን ፲፱፻፹፮ አዲስ አበባ ላይ እንዲደረግ በመወሰንና አስተባባሪ ኮሚቴ መርጦ በመሰየም ስድስት ነጥቦችን ያዘለ ጥሪ በማስተላለፍ ተቋጭቷል።

አገዛዙ ይኸንን ጉባዔ ከጅምሩ በንቀት ዓይንና በትዕቢት የተመለከተው ቢሆንም ስብስቡ በቀላሉ የሚበተን እንዳልሆነና ምን ያኸል ጠንካራና የምር ተፈታታኝ መሆኑን ሲረዳ መወራጨቱን የጀመረው ዶ/ር በዬነን ከሽግግሩ ምክትል ሚኒስትርነት ሥልጣን በማባረር ነበር።

ምንም እንኳን ይኸ ጉባዔ በውጭና በውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን አንድ ላይ አምጥቶ በአንድ የጋራ ዓላማ ሥር አሰባስቦ በአንድ የጋራ መዋቅር አካትቶ ለመሥራት ጥረት የተደረገበት፣ በተሣታፊዎች ዘንድም ለጋራ ዓላማው እውን መሆን የመታገያ ነጥቦች ላይ ስምምነት የተደረሰበትና ደፈናዊ በሆነ መንገድ ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የሰላምና እርቅ ጉባዔ ኢትዮጵያ ውስጥ (አዲስ አበባ) አካሂዶ አገዛዙን በጨመረ ሁኔታ አዲስ የሽግግር ሂደት

መጀመርን እንደ ግብ የወሰደ ቢሆንም፤ አንደኛ ብዙዎቹ ተሣታፊዎች አዲስ በመሆናቸውና ቀደም ሲል የማይተዋወቁ በመሆኑ እንዲሁ ከአደረጃጀት ዘይቤአቸው መገማመት ሊኖር ቢችልም የአስተሳሰብና የአመለካከት፣ የዓላማና የራዕይ መጣጣም ያልነበራቸውና እነኝኽንም ልዩነቶች ለማጥበብ እንዲቻል ለመጠናናትና አንዱ ሌላውን ተረድቶ ተገቢ መግባባትን ለማዳበር በቂ ጊዜ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ጉባዔው ሲያልቅ ለጋራ ውሳኔዎች ተገዥ ለመሆንና ስምምነቶችን በጋራ ተግባራዊ ለማድረግ በተሣታፊዎች መኻል መኖር የሚገባው ሙሉ መተማመን ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ሁለተኛ በተሣታፊዎች ዘንድ ከነበረ በጎ-ፈቃድ ውጭ የአገዛዙን መሠረታዊ የፖለቲካ ፍልሥፍናና ይበልጥ አምባ-ገነናዊ እየሆነ የሚሄድ ተፈጥሮው ላይ በጥልቀትና በተገቢ ግንዛቤ የተወሰደበት አልነበረም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን በጊዜው በአገር ውስጥ ያለው ሁኔታ እንዲቀየር በተሣታፊዎች ዘንድ በጎ-ፍላጎት ቢኖርም፤ ብዙዎቹ ተሣታፊዎች ከስብሰባ ሲወጡ ወደ ስብሰባ ይዘውት ከመጡት አስተሳሰብና አመለካከት የተለዬ ወይም የተቀየረ ይዞታ ላይ ነበሩ ማለት አይቻልም፡፡ በድርጅቶች መኻል ቅድመ-ጉባዔ የነበረው እርስ-በርስ የመጠራጠርና በቀና ያለመተያየት ይዞታ ድኅረ-ጉባዔም ቁጭ እንዳለ ነው አገዛዙ አፍንጫ ሥር አስገዳጅነት ያለው ጉባዔ አድርጎ በትዕቢት በተወጠሩ አፍላ ጉልበተኞች የሚመራ ኢሕአዴግን ትርጉም ወደ-አለው ድርድር ለማምጣት ታስቦ እንቅስቃሴ የተደረገው፡፡

ያም ሆኖ ግን ይኽ የሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ ጉባዔ አስተባባሪ ኮሚቴ የጉባዔውን ውሳኔዎች በተግባር እንዲተረጎም በአገር ውስጥ ቅርንጫፍ በማቋቋም አገር-አቀፍ የሰላምና የእርቅ ጉባዔ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲጠራ የተወሰነው ውሳኔ በተባለው ጊዜ እውን እንዲሆን ከፍተኛ መረባረብ አድርጓል፡፡ አገር-አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባዔውን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ሰነዶችንና ግንዛቤ አስጨባጭ የቅስቀሳ ጽሑፎችን በማዘጋጀት፣ አባል ድርጅቶች ከጋራ አቋማቸው ሳያፈናግጡ እንዲቆዩ በማግባባት፣ የንዋይ (ገንዘብ) እና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በማሰናዳት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሙያ ማኅበራትና ስብስቦች፣ ወዘተ... የአገዛዙን ልዩ ልዩ ጫናዎች ተቋቁመው በጉባዔው ላይ እንዲገኙ በማሳመን፣ ለዚኽም "በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባዔ የሽማግሌዎች ኮሚቴ" እንዲቋቋም በማድረግ አገዛዙን ጨምሮ ሁሉም ኃይሎች በዚኽ ጉባዔ ላይ እንዲገኙ የማሳመንና የማግባባት ሥራ እንዲሠራ በማድረግ፣ የውጭ ኃይሎችና ተቋማት ስለ ጉባዔው ዓላማ እንዲገነዘቡና ድጋፋቸውን እንዲለግሱ ጥረት በማድረግ ከፍተኛ መረባረብ አድርጓል፡፡

ያንን ማድረግ በመቻሉም በአንድ በኩል ለውጥ ፈላጊው ኃይል ከተባበረ ለውጤት መብቃት እንደሚችልና በሌላ በኩል የአገዛዙን እውነተኛ አምባ-ገነናዊ ባኅሪይ በገሃድ እንዲጋለጥና "ዴሞክራሲያዊነቱም" ይስሙላዊ እንደሆነ ማሳየት የቻለ ጉባዔ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም 'ፓሪስ አንድ' የገጠሙትንና የውጭና የውስጥ አሉታዊ ጫናዎች ተቋቁሞ ጉባዔው ያለመውን የቅርብ-ጊዜ ግብ ለመምታት የቻለና ውጤት ያስመዘገበ፣ ያም የተለያዩ አቋሞችና እምነቶች የያዙ ድርጅቶች በጋራ ቢሠሩ ለጋራ ውጤት እንደሚበቁ ያስመሰከረና በአገር-ውስጥም ይሁን ከአገር-ውጭ የሚገኙ ድርጅቶች አንድ ላይ ለመታገል እንደሚችሉ በተግባር ያረጋገጠ ፈር-ቀዳጅ ስብስብ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

<u>ሐ - ፫፤- የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት (ኢሰዴአኃ)፤</u>

ከመጋቢት ፪ እስከ ፬ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም (March 11-13, 1993) ፓሪስ ላይ በተደረገው 'ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ' ጉባዔ ላይ በተወሰነው መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የሰላምና እርቅ ጉባዔ እንዲጠራ አስተባባሪ ኮሚቴ መሰየሙና ያም አስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ በአገር ውስጥ ትኩረት ሰጥቶ ጉባዔውን የሚያዘጋጅ ቅርንጫፍና ልዩ ልዩ አካላትን ማቋቋሙ ይታወሳል፡፡ በውሳኔው መሠረት .....

***በክፍል ስምንት ይቀጥላል.....***